# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም:-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ
**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## <u>ዜና ዘገባ</u>

**ሚያዚያ 13 ቀን 2005 ዓ.ም**

**የጋምቤላ ክልል ፕሬዘዳንቱን ጨምሮ ስድስት የክልሉ ስራ አስፈጻሚዎች ከስልጣናቸው ተባረሩ፤ፕሬዝዳንቱ አዲስ አበባ ውስጥ በቁም እስር ላይ ነው ተባለ**

**በቢኒሻንጉል ክልል የወያኔ መሪዎች የሰጡትን ትዕዛዝ ያስፈጸሙ የዞኑንና የወረዳ ባለስልጣናት ከስልጣናቸው ተባረሩ በቅርቡም ዘብጥያ ይወርዳሉ ተባለ፤**

**ዘረኛው የወያኔ ቡድን አገዛዝ ያስመረራቸው ምሁራን እና ባለሀብቶች ሀገር ጥለው እየተሰደዱ መሆኑ ታወቀ፤**

**በአፋር እና በቦረና የሚገኙ አርብቶ አደሮች በተፈጠረው ድርቅ የተነሳ እያለቁ መሆኑ ተጋለጠ፤**

**የኢሉአባቦራ ዞን የያዮ ወረዳ ደን ቃጠሎ ምሥጢር ተጋለጠ፤**

በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍል ውስጥ የወያኔን ስርዓት ለመጣል በትጥቅ ትግል እየተፋለመ ነው ተብሎ እየተነገረለት ካለው የጋምቤላ ሕዝቦች ነጻነት ንቅናቄ (ጋሕነን) ጋር ግንኙነት አላችሁ የተባሉ ከፍተኛ የክልሉ ባለስልጣናት ከስልጣን እየተባረሩ መሆኑ ታወቀ::

ባለፈው ወር መጀመሪያ ላይ በጋምቤላ ክልል ውስጥ ታጣቂ ኃይሉ በሰነዘረው ድንገተኛ ወታደራዊ ጥቃት ጉዳት ማድረሱን ተከትሎ የወያኔ መሪዎች ከክልሉ ባለስልጣናት መከከል አንዳንዶቹን በመተካካት ስም ሲያባርሩ ሌሎቹን ደግሞ እያሰሩ ማዕከላዊ ምርመራ ያስገቧቸው መሆኑ ከደረሰን ዜና ለማወቅ ተችሏል::

የሆኑት የክልሉ የፀጥታ ዘርፍ ኃላፊና የፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር የሆኑትን ሁለት ቱባ የአኘ ዋክ ብሄር ተወላጅ ባለስልጣናት ከቢሮዋቸው ለስራ ትፈለጋላችሁ በሚል በህወሀት የደህንነት ኃይሎች ተይዘው ቀጥታ ወደ አዲስ አበባ ማዕከላዊ ምርመራ እስር ቤት እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን

እነሱን ተከትሎ በክልሉ በርካታ የዞንና የወረዳ ባለስልጣናትም እየታፈሱ ለእስር በመዳረጋቸው መንግስታዊ መዋቅሩ ለአንድ ወር ከሳምንት ያህል  ስራ አቁሞ እንደነበር ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ይገልጻል::

በጋምቤላ ክልል አንዳንደ የክልሉ ባለስልጣናት መባረራቸውንና  እና መታሰራቸውን ተከትሎ የክልሉ ፕሬዝዳንት የሆነው ኡሞድ ኡቦንግ ከስልጣኑ ከመነሳቱም በተጨማሪ ለስራ ትፈለጋለህ ተብሎ አዲስ አበባ ተጠርቶ ለጥቂት ቀናት በማዕከላዊ እስር ቤት ከተደረገ በኋላ መለቀቁን ለማወቅ ችለናል::

ከእስር ከተለቀቀ በሁዋላም  መተካካት በሚል በይፋ ከፕሬዝዳንትነቱ የተነሳ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ለቁጥጥር እንዲመች እና በቁም እስር እንዲሆን ተብሎ በፌዴራል መስሪያ ቤት ውስጥ ተመድቧል ይባል እንጅ  ይሄ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ድረስ ስራ ያልጀመረ መሆኑ ታውቋል::

ኡሞድ ኡቦንግ የተባለው  ግለሰብ በ1996  ዓ.ም የወያኔ ቡድን በጋምቤላ በአኙዋክ ብሄር ተወላጆች ላይ የጅምላ ጭፍጨፋ እርምጃ በወሰደበት ወቅት የጸጥታ ዘርፍ ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ የነበረ ሲሆን በወቅቱ ለተፈጸመው ጅምላ ጭፍጨፋ ተጠያቂ ለማድረግ ሙከራ የተደረገ ቢሆንም ግለሰቡ ለጅምላ ጭፍጨፋ መጠየቅ ካለበት መለስ ዜናዊ እንጂ እኔ አይደለሁም በማለት መልስ በመስጠቱ ለዓመታት ጥርስ ተነክሶበት ቆይቶ አሁን ግዜውን ጠብቆ ከጋህነን ጋር ግንኙነት አለህ ተብሎ ከፕሬዝዳንትነቱ መነሳቱን ይሄው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

የወያኔ ቡድን ወደ ስልጣን ከወጣ ግዜ ጀምሮ ከዝቅተኛ ኃላፊነት ቦታ እያደገ የመጣው ኡሞድ ኡቦንግ ፕሬዝዳንት ሆኖ ከመሾሙ በፊት የክልሉ የጸጥታ ቢሮ ኃላፊ...የክልሉ የፖሊስ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር እና በሁዋላም ኮሚሽነር ሆኖ ያገለገለ ሲሆን አሁን በመተካካት ስም ከፓርቲው ምክትል ሊቀመንበርነት እና ከክልሉ ፕሬዝዳንትነት ስልጣኑ ሲነሳ በምትኩ ምክትል ፕሬዝዳንት የነበረው ጋትሉዋክ ቱት የተባለው እንደተሾመ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል::

የጋምቤላ ክልል የስራ ቋዋንቋዋ የፌዴራሉ ቋንቋ በመሆኑ አማርኛ መናገር የሚችሉ የህወሀት አባሎች ከትግራይ እና ከአዲስ አበባ ተዛውረው አዲስ ከተሾሙት የአኙዋክ እና ኑዌር ባለስልጣናት ስር አማካሪ ሆነው እንዲሰሩ መመደባቸውንም ይሄው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

በአሁኑ ሰዓት በጋምቤላ ክልል ከባለስልጣናት መባረር..... መታሰር እና መሰደድ ጋር በተያያዘ መረጋጋት የሌለ ከመሆኑም ባሻገር ስራ ሙሉ ለሙሉ መቆሙንም የደረሰን ጥቆማ ጨምሮ ገልጾዋል::

በሌላ ዜና ለዘመናት ከኖሩበት ቀዬ የአማራ ብሔር ተወላጆችን  እንዲፈናቀሉ ያደረጉት የወያኔ ባለስልጣናት በደረሰባቸው ተቃውሞ የተነሳ ግልገል ሹማምንቱን ተጠያቂ አድርገው ለፍርድ ሊያቀርቡዋቸው መሆኑን ከቤንሻንጉል ክልል ከአሶሳ ከተማ የደረሰን ጥቆማ አጋለጠ::

በዚሁ ክልል በመተከል እና በካማሽ ዞን ሲኖሩ የነበሩትን የአማራ ብሔር ተወላጆች አሰቃቂ ግፍ በተሞላበት ሁኔታ አስገድደው እንዲፈናቀሉ ያደረጉ ናቸው የተባሉ የዞንና የወረዳ ባለስልጣናት ለህግ መቅረብ አለባቸው ተብሎ ሰሞኑን በክልሉ እሩጫ መጀመሩን ከአከባቢው ከሚደርሱ ዜናዎች ለማወቅ ተችሏል::

ከወያኔ ቁንጮ ባለስልጣናት ከህወሀቶቹ እስከ ብአዴኖቹ ድረስ መክረው እና ዘክረው በምስጢር ትዕዛዝ ሰጥተው ተግባራዊ ያደረገው የክልሉ ፕሬዝዳንት አህመድ ናስር የተባለው ግለሰብ ሳይጠየቅ በተዋረድ ትዕዛዝ የደረሳቸው የበታች ባለስልጣናት ተጠያቂ እንዲሆኑ መደረጉ ወያኔ ለዓለም አቀፍ ረጂዎቹ ፍትሀዊ ለመምሰል ያደረገው መፍጨርጨር ነው የሚሉ ዜጎች ብዙ መሆናቸው ታውቆዋል።

ወያኔ እንደ አገዳ መጥጦ መጣል የተካነ ቡድን መሆኑን ያልተረዱና ማገናዘብ ያልቻሉ የዞንና የወረዳ ባለስልጣናት ለሆዳቸው ሲሉ ባለስልጣናቱ የሰጡትን ትዕዛዝ ተግባራዊ ማድረጋቸው ሳያንስ የሰውን ልጅ እንደ እንስሳ በጭነት መኪና ጠቅጥቀው ከማባረራቸውም በተጨማሪ ያፈሩትን ሀብት እንዳይጠቀሙበት በእሳት እየለኮሱ ማቃጠላቸውን ጨምሮ አስገድዶ መድፈር ድረስ ግፍ ሲፈጽሙ እንደነበርም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል።

የወያኔ ባለስልጣናት በግልገል ሹምንቱ ላይ ጣታቸውን በመቀሰር ወንጀለኛ መሆናቸውን በሚቆጣጠሩት ሚዲያ በይፋ ያወጁ ሲሆን በተለይ የካማሽ ዞን አስተዳዳሪን ጨምሮ የወረዳዎቹን አመራሮች በሙሉ ከስልጣናቸው እንዲነሱ ተደርጎ ጉዳያቸው ወደ ፍርድ ቤት እንዲገባ በመደረጉ በወያኔ ውስጥ አሁንም ሌላ ትርምስ የተፈጠረ መሆኑን አንዳንድ ዜናዎች ይጠቁማሉ።

የካማሽ ዞን ዋና አስተዳዳሪ የነበረውና መፈናቀሉን ከክልሉ ፕሬዝዳንት አሕመድ ናስር ጋር እጅና ጉዋንት ሆኖ ሲመራ ነበር የተባለው መልከጅ ባጋሎን ዓርብ ሚያዚያ 4 ቀን 2005 ዓ.ም በይፋ ከስልጣኑ እንዲነሳ የተደረገ ሲሆን ሌላኛው ያልጠገበው አበበ ዱቤ የተባለው ካድሬ በቦታው መመደቡን ከስፍራው የደረሰን ዜና ይገልጻል።

በአሁኑ ሰዓት ወደ ነበሩበት ስፍራው እየተመለሱ ያሉት ዜጎች በቤት ውስጥ የነበራቸው እህልና እና ሌሎች ቁሳቁሶች ሙሉ ለሙሉ ስለወደሙባቸው የዕለት ጉርስ አጥተው ለከፍተኛ ችግር ከመዳረጋቸውም ባሻገር ለጠፋባቸውና ለተቃጠለባቸው ንብረት መተኪያ የሚሆን አንድም ድጋፍ እንዳልተደረገላቸው ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል።

ወያኔ ሆን ብሎ በሰራው ወንጀል እራሱ መልሶ በመደንገጥ ለተፈናቀሉት ወገኖች መቋቋሚያ ይሰጣቸዋል እያለ የገዛ ካድሬዎቹን እና መላውን ሕዝብ ለማታለል ሀሰተኛ ፕሮፓጋንዳ እየነዛ ቢሆንም እስከ አሁን አንዳችም ድጋፍ ያላደረገላቸው መሆኑን የችግሩ ገፈት ቀማሾች አጋልጠዋል።

በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመተከል እና በካማሽ ዞን ውስጥ ይኖሩ የነበሩት የአማራ ብሔር ተወላጆች ባዶ እጃቸውን የተባረሩ መሆኑ እየታዋቀ የካማሽ ዞን ብቻ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ሲደረግ ከመተከል የተባረሩት ግን አሁንም ፍኖተ ሰላም እና በሌሎች ከተሞች ተበትነው እንደሚገኙ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል።

በአማራ ብሔር ተወላጆች ላይ ብቻ ተነጥሎ የተወሰደው የግፍ እርምጃ የዘር ማጥፋት ወንጀል በመሆኑ ወደ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት ለመውሰድ ዝግጅቱን አጠናቅቄያለሁ ሲል በኢንጅነር ኃይሉ ሻውል የሚመራው መኢአድ ሰሞኑን በይፋ ገለጠ።

ዜጎቹ ከኖሩበት ቀዬ እንዲፈናቀሉ የተደረጉት በፌዴራል ባለስልጣናት ትዕዛዝ መሆኑን ጠቅሶ የደረሰባቸውን በደል እና ግፍ የሚያጋልጥ የሰው እና የቪዲዮ ማስረጃ በእጃችን ስለገባ በቅርቡ ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እናመራለን ሲል ገልጾዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ወያኔ በዘረጋው አፋኝ ስርዓት የከፋ ችግር የደረሰባቸው በተለያዩ ሙያ ተሰማርተው ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን ሲያገለግሉ የነበሩ ዜጎች እየተሰደዱ መሆናቸውን ከተለያዩ መስሪያ ቤቶች ከገኘናቸው መረጃዎች ለማወቅ ችለናል።

በተለያዩ ሙያዎች ተሰማርተው  ሀገርና ሕዝብን ሲያገለግሉ የነበሩ ወገኖች ለ በወያኔ አምባገነን ቡድን በሚደርስባቸው ጫና እና በደል የተነሳ ከሚወዱት ሕዝባቸውና ሀገራቸው ሳይወዱ በግድ እየተነጠሉ ከመጥፋታቸውም ባሻገር በሌሎች ሀገራት ጥገኝነት እየጠየቁ መሆኑ ታውቆዋል።

ሰሞኑን የህክምና ባለሙያ የሆኑ ዶክተሮች የወያኔ ቡድን  በሚያደርስባቸው ፖለቲካዊ ጫና ምክንያት  ህዝባቸውን እና ሀገራቸውን ጥለው የተሰደዱ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በሀገር ውስጥ በተፈጠረው የሀኪም እጥረት በሽተኞች በቂ የህክምና እርዳታ ለማግኘት አለመቻላቸውንም በሙያው የጠለቀ እውቀት ያላቸው ወገኖች ሲናገሩ ተደምጠዋል።

በዚህም መሰረት ከራስ ደስታ..... ከጳውሎስ...... ከምኒልክ ሆስፒታሎች አራት ዶክተሮች በመሰደዳቸው የእነሱን ቦታ የሚሸፍን ሀኪም በመጥፋቱ ህሙማኖች በየሆስፒታሉ ያለ ህክምና እየተንከራተቱ የሚገኙ መሆናቸው ታውቋል።

ከሕክምና ሙያ በተጨማሪ በጋዜጠኝነት ሙያ ላይ ተሰማርተው ሲሰሩ የነበሩ የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞችም ላይ በሚደርሰው ይህ ቀረሽ የማይባል ግፍ ...እንግልት እና መከራ የተነሳ  ሀገር ጥለው እየተሰደዱ ነው።

ከዚህ ቀደም በወያኔ ባለስልጣናት ትዕዛዝ ከህትመት ውጭ እንድትሆን የተደረገችው የፍትሕ ጋዜጣ ስራ አስኪያጅ ጋዜጠኛ ማስተዋል ተደራራቢ ክሶች ቀርበውበት እየተከራከረ ባለበት በአሁኑ ሰዓት የወያኔ ደህንነቶች በሕይወቱ ላይ አደጋ ሊያደርሱበት መሆኑን በመረዳቱና ቀድሞ በማወቁ ሀገሩን ጥሎ ለመሰደድ እንደተገደደ ለቤተሰቦቹ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ተናግረዋል።

አብሮት ከሚሰራው ከስራ ባልደረባው ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ጋር አራት ክሶች ቀርቦባቸው በከፍተኛው ፍርድ ቤት እየተመላለሱ ባለበት በዚህ ግዜ የወያኔ ደህንነቶች ብርቱ ክትትል እያደረጉባቸው መውጫ እና መግቢያ ከመሳጣታቸውም ባሻገር ለሕይወቱ አስጊ ስለሆነ ከሀገር ሊሰደድ እንደቻለ እነዚሁ ለቤተሰቦቹ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ተናግረዋል።

በጋዜጠኛ ማስተዋል ዋና ስራ አስኪያጅነት ሲመሩ የነበሩት ፍትህ ጋዜጣና አዲስ ታይምስ መጽሄት በወያኔ ባለስልጣናት ትዕዛዝ ከህትመት ውጭ እንዲሆኑ ተደርጎ ልዕልና የተሰኘች ጋዜጣ ከአሳታሚ ድርጅቱ በኪራይ ወስደው በመስራት ላይ እንዳሉ በድጋሚ ለሶስተኛ ግዜ እንዲቋረጥ

የተደረገ ቢሆንም በጋዜጠኞቹ ላይ በየቀኑ በሚደርሰው ወከባና እንግልት ምክንያት የተነሳ ጋዜጠኛው ሀገር ጥሎ መኮብለሉ ታውቆዋል::

በቅርቡ ተመስርቶ ትግል የጀመረው ሰማያዊ ፓርቲ አመራሮች ላይም ተመሳሳይ የወከባ እና የአፈና እንቅስቃሴ በመጀመሩ የድርጅቱ የወጣቶች ጉዳይ ኃላፊና የህዝብ ግንኙነት አባል የሆነው ወጣት አርአያ ጌታቸውም ሀገር ጥሎ የተሰደደ መሆኑን የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች ገልጸዋል::

ወያኔ በሚያደርሰው አፈና ከምሁር እስከ ነጋዴ .....ከአዛውንት እስከ ወጣት ......ከሴት እስከ ወንድ...... ከጋዜጠኛ እስከ ፖለቲከኛ ድረስ ሁሉም ነፍሳቸውን ለማዳን ሲሉ የሚወዱትን ሀገራቸውንና ህዝባቸውን ጥለው እየተሰደዱ በሰው ሀገር ጥገኛ ለመሆን እንደተገደዱ ብዙዎቹ ካሉበት ሆነው እየተናገሩ ይገኛሉ::

በያዝነው ዓመት ውስጥም በውጭ ሀገር አጠራቅመው ያመጡትን ሀብት በሀገራቸው ስራ ፈጥረው ሊሰሩ የሞከሩ እጅግ ቁጥራቸው የበዙ ዜጎች በወያኔ አምባገነን ቡድን በሚደርስበቸው ጫና ምክንያት ሀብት ንብረቶቻቸውን ጥለው ተሰድደው ወደነበሩበት ሀገር የተመለሱ መሆኑንመ ከተገኘ ው መረጃ ለማወቅ ተችሏል::

ለመጀመሪያ ግዜ የቤት መኪኖችን በሀገር ውስጥ መገጣጠሚያ ፋብሪካ ያቋቋቋመው ኢ/ር ታደሰ የተባለው የሆላንድ ካር ፋብሪካ ባለቤት ከወያኔ ባለስልጣናት ጋር ባለመግባባቱና አባል ባለመሆኑ ብቻ በተደጋጋሚ የሚደርስበትን ጫና ተቋቋቁሞ ለመስራት ቢሞክርም በቅርቡ ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት ከሀገር ወጥቶ ቀድሞ ወደነበረበት አውሮፓ መሰደዱ ታውቆዋል::

በተመሳሳይ በኢትዮጵያ ውስጥ ሀይ ላንድ የተሰኘ የመጀመሪያውን የታሸገ ውሀ ለገበያ ያቀረበው አቶ ኤርሚያስ አመልጋ የተባለው ባለሀብት የተለያዩ ፋብሪካዎችን መስርቶ ሲሰራ የቆየና በቅርቡ ደግሞ ዘመን ባንክ እና አክሰስ ሪል ስቴትን አቋቋቁሞ በከፍተኛ ፍጥነት እድገት ማሳየቱ በወያኔ ቡድን ስላልተወደደለት ከሀገር እንዲወጣ መደረጉ ለግለሰቡ ቅርበት ካላቸው ወገኖች ለማወቅ ችለናል::

በተያያዘ ዜና የወያኔ ቡድን በዘረጋው የከፋፍለህ ግዛ ፖለሲ ምክንያት ዜጎች ተወልደው ባደጉበት ቀዬ ሰርተው እንዳይኖሩ ለማድረግ እና ለልማት በሚል ሰበብ እያፈናቀላቸው በመሆኑ በሚሊዮን የሚቆጠሩት በርሀብ እየሞቱ መሆኑን ከቦረና እና ከአፋር ክልል የደረሰን ጥቆማ ገለጸ::

በአፋር ክልል በተለያዩ ዞኖች እና ወረዳዎች ውስጥ ባለፉት ሶስት ወራት በክልሉ በተፈጠረ ርሀብ ምክንያት ከ25 ሰዎች በላይ የሞቱ ሲሆን በአሁኑ ሰዓትም ከፍተኛ ርሀብ በክልሉ በመኖሩ እጅግ ቁጥራቸው የበዙ ዜጎች ወደ አጎራባች ከተሞች እየተሰደዱ መሆኑ ታውቆዋል::

ወያኔ ልማት አመጣሁ...አርሶ አደሩን ሚሊየነር አደረግኩኝ ...አርብቶ አደሩን ከዘላንነት ኑሮ አውጥቼ ከፊል አርብቶ አደር አደረኩት እያለ የዓለምን ሕዝብ እያታለለና የለጋሽ ሀገራትን እየሸነገለ ባለበት በዚህ ግዜ በሀገሪቱ በተፈጠረ ርሀብ ምክንያት ከ25 ሰዎች በላይ ሲሞቱ እጅግ ቁጥራቸው የበዙት

ደግሞ ለከፋ ስቃይ ተዳርገው እንደሚገኙና አቅም ያላቸው ዜጎች ደግሞ ወደ አጎራባች ከተሞች እየተሰደዱ መሆኑ ከስፍራው ደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

በአፋር ክልል ተወላጁ ከኖረበት ቀዬ ስኩዋር ፋብሪካ ለመገንባት በሚልና ለሸንኮራ ተክል እርሻ ተብሎ ሕዝቡ ያለ አንዳች ካሳ ክፍያ እንዲፈናቀል ተደርጎ ያለፈውን ዓመት አንድም እህል ሳይዘራ ያሳለፈ በመሆኑ ዘንድሮ ዝናብ ከመቋዋረጡ ጋር ተያይዞ ርሀብ በመከሰቱ ዜጎች እየረገፉ መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

የወያኔ ቡድን ዓመቱን ሙሉ የተለያዩ በዓላትን አከበርኩ እያለ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ በቢሊዮን የሚቆጠር ብር እያባከነ ዜጎች የሚልሱትና የሚቀምሱት አጥተው በርሀብ ምክንያት እየረገፉ ባለበት በዚህ ግዜ ችግር እንደተፈጠረ አንድም ቀን ለመግለጽ አለመፈለጉና የእርዳታ ጥሪ አለማቅረቡ ለጋሽ ድርጅቶችን ለማታለል ቢሆንም ለሕዝብ ደንታ እንደሌለው በግልጽ የሚያሳይ ነው በሚል ብዙዎቹ ይተቻሉ::

በአፋር ክልል የተከሰተው ርሀብ መፍትሄ እየተባባሰ ባለበት ባሁኑ ወቅት በቦረና ዞንም ከፍተኛ ድርቅ ተከስቶ ከብቶች እያለቁ መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ይገልጻል::

በቦረና በየዓመቱ በአርብቶ አደሮች ላይ ከፍተኛ ርሀብ እንደሚከሰት የሚያውቁት የወያኔ ቡድን መሪዎች አስቀድመው መጠባበቂያ የእህል ክምችት ወደ ስፍራው ሳይወስዱ በመቅረታቸው ሕዝቡም ሆነ ከብቶች በከፍተኛ ድርቅ ተጠቅተው እንደሚገኙ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

በቦረና ዞን ውስጥ ታጣቂ የተቃዋሚ ኃይል ይንቀሳቀስበታል.....ከእኛ ጎን ሆናችሁ ታጣቂውን ልትፋለሙ ዝግጁ አይደላችሁም...... እናንተም ከታጣቂ ኃይሉ ጋር ትወግናላችሁ .....እያሉ ሕዝቡን ብዙ ግዜ የቁም ስቅሉን ከማሳየታቸውም በተጨማሪ ርሀብ እና ድርቅ በሚከሰትበት ወቅት እርዳታ ከመስጠት ይልቅ በህዝቡ እያፌዙበት እንደሆነም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

በአሁኑ ሰዓት በቦረና የሚገኙ አርብቶ አደሮች በተፈጠረው ድርቅ የተነሳ ከብቶቻቸው እየሞቱባቸው እና ልጆቻቸውንም የሚያበሉት በማጣታቸው በከፍተኛ ችግር ውስጥ ወድቀው የሚገኙ ሲሆን እርዳታ የሚሰጣቸው አፋጣኝ ለጋሽ ድርጅት ይድረስልን እያሉ ሲማጸኑ እንደነበርም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

በባህር ዳሩ 9ኛ ጉባኤ ላይ የወያኔ ቡድን የዘረጋው የግብርና መር ፖሊሲ ችግር እንዳለበት አስመልክቶ የግብርና ሚኒስትሩ ተፈራ ደርበው የተባለው የብአዴን ወጣት ካድሬ ከውጭ ቀድተን ያመጣንለት የግብርና ዘዴ ከሀገራችን ተጨባጭ እውነታዎች ጋር የማይጣጣሙ በመሆኑ አርሶ አደሩ ከውጤቱ ይልቅ ውድቀቱ ያመዘነበት ስለሆነ ቆም ብለን እራሳችንን ልንመረምር እና ልንፈትሽ ይገባል ብሎ ሀሳብ በመሰንዘሩ የተበሳጩና እውነታው እሬት የሆነባቸው የብአዴኑ በረከት ስምኦንና የህወሀቱ ሊቀመንበር አባይ ወልዱ እየተፈራረቁ የአፈጻጸም እንጂ የፖሊሲ ችግር የለብንም ይሄን ደግሞ በሂደት ልንቀርፈው የምንችለው ነው በማለት ሲሙዋገቱ እንደነበር መዘገባችን አይዘነጋም::

በመጨረሻም የወያኔ ቡድን ለም እና ሰፊ የእርሻ መሬቶችን ለውጭ ሀገር ባለሀብቶች ለመቸብቸብ እያለ ዜጎች እትብታቸው ከተቀበረበት እና ልጅ ወልደው ከዳሩበት ቀዬ እያፈናቀለ ከመሆኑም በተጨማሪ በቅርቡ ደግሞ ደኖችን እያቃጠለ መሆኑ ተጋለጠ፡፡

ሰሞኑን በኦሮሚያ ክልል በኢሉአባቦራ ዞን በያዮ ወረዳ ገርባ ተብሎ የሚጠራውን ደን ለውጭ ባለሀብቶች መሬቱን ለመሸጥ ሲል ደኑን በእሳት ለኩሶ ማጋየቱን የግብርና ሚኒስትር መስሪያ ቤት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አጋለጠ፡፡

በሀገሪቱ አሉ ከሚባሉት ጥቂት ደኖች መሀከል የሚታወቀው ይሄው የገርባ ወንዝ ደን ባለፈው ሳምንት ወያኔ በለኮሰው እሳት ሙሉ ለሙሉ የወደመ ሲሆን ድርጊቱን እራሱ የፈጸመው በመሆኑ ለእርዳታ ከሰባት ቀናት በሁዋላ መምጣቱ ስራውን ያጋለጠ መሆኑን የግብርና ሚኒስትር ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

የአካባቢውን ነዋሪዎች ዋቢ አድርገው የገለጹት የግብርና ሚኒስትር ምንጮች እንዳሉት ከሆነ ከአያት ቅድመ አያቶቻቸው ጀምሮ ደኑን እንደ ወለዱት ልጅ ሲንከባከቡት እንደኖሩና ከ60 ዓመት በላይ አንድም ግዜ ቃጠሎ ተከስቶ እንደማያውቅ ጠቅሰው አሁን ግን ሆን ተብሎ ጋዝ ተርከፍክፎ በምስጢር መቃጠሉን ሕዝቡ እያለቀሰ ሲናገር እንደነበር ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

ደኑን ከማፍቀር የተነሳ የአካባቢው ሕዝብ በደኑ እየማለ የሚገኝ ሲሆን አልፎ ተርፎ እንደ ጣኦት ሁሉ ያመልከው እንደነበር የገለጹት ምንጮቹ የወያኔ ቡድን ቦታውን ለውጭ ሀገር ባለሀብቶች ለመሸጥ ስለፈለገ ሚያዝያ 2 ቀን 2005 ዓ.ም ሌሊቱን ጋዝ አርከፍክፎ እንዲቃጠል ማድረጉን ነዋሪዎቹን ዋቢ አድርገው ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

የአካባቢው ነዋሪዎች ደኑ በእሳት ተቀጣጥሎ መንደዱን ያዩት ከሰዓታት በሁዋላ በመሆኑ በቀላሉ ሊቆጣጠሩት ሳይችሉ የቀሩና ከአቅማቸው በላይ በመሆኑም ለእርዳታ የክልሉን እና የፌዴራል መንግስቱን ጥሪ ቢያቀርቡም ከሰባት ቀናት በሁዋላ 700 ወታደሮችን ብቻ መላካቸው አስገራሚ ድራማ ነው ሲሉ ነዋሪዎቹ ሲናገሩ እንደነበር ምንጮቹ ተናግረዋል፡፡

የወያኔ ባለስልጣናት ደኑ በእሳት ተቀጣጥሎ መውደሙን ሲያረጋግጡ 700 የመከላከያ ወታደሮችን እና የፌዴራል ፖለሶችን ወደ ስፍራው የላኩ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ አንድ የጦር ሄሊኮፕተር አሰማርተው የማጥፋት ሙከራ አደረግን ቢሉም ደኑ ቀድሞውኑ ወድሞ ያለቀ በመሆኑ አንዳችም ድጋፍ ሊያደርጉ አለመቻላቸው አስቀድሞ የታቀደውን መፈጸማቸው ተረጋግጦዋል እያለ ሕዝቡ እያነባ ሲናገር መደመጡን ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡